## "ሲኖዶስና" የቀሳጥያን ጥያቄ!

"ሲኖዶስ" አባ ማትያስ እንዲያስፈጽሙ የሚሰጣቸውን ውሳኔ አባ ማትያስ በገዛ ፈቃዳቸው ከሕገ ቤተክርስቲያን ውጭ እየሻሩና እየቀለበሱ በምትኩ ቤተክርስቲያንን የሚጎዳ ሕገ ወጥ የውንብድና ተግባር እየፈጸሙ የቀጠራቸውን አካል ማለትም ወያኔንና መናፍቃኑን ተጠቃሚ የሚያደርግ ተግባር ላይ ተጠምደው ቢያስቸግሩት ሲኖዶሱ በእግዚአብሔር ቃል ሊመክር ሊገስጽ ቢሞክርም አልገሰጽ አልዳኝ አልሸመገል ብለው ቢያስቸግሩ ጊዜ ሰውየው ከሀዲና እምነት አጉዳይ የቤተክርስቲንን አደራ በላ ሆነው መታመን አልቻሉምና ሲኖዶሱ የሚያስተላልፋቸውን ውሳኔዎች በትክክል መፈጸማቸውን የሚከታተል የሚቆጣጠርና የሚያስፈጽም እንደራሴ መሠየም ወይም መሾም አስፈለገውና በዘንድሮው የርክበ ካህናት "ቅዱስ ሲኖዶስ" ምልዓተ ጉባኤ ላይ ጉዳዩን አነሣው ፡፡

አባ ማትያስ ግን "በሕጉ እንደራሴ ይመደብ የሚል ሕግ የለም፤ ከሕጉ ውጭ ነው፤ ሕጉ ይከበር፤ እኔስ ምን አደረኳቹህ? እየሠራሁ አይደለም ወይ? ከእኔ በላይ ሌላ አለቃ፣ ሌላ ባለሥልጣን ልታስቀምጡ ነው ወይ?" በማለት ክችች አሉ፡፡ ይሄንን ያለ ሰው ለቤተክርስቲያን መታመን ነበራ!

"የሲኖዶስ" ምልዓተ ጉባኤውም " ሲኖዶስ ሕግ የማውጣት፣ የወጣውን የማሻሻልና የመሻር ከፍተኛ ሥልጣን አለው፤ ውሳኔውም እንደ ሕግ ይሠራል፤ የቅዱስነትዎም ተጠሪነት ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው፤ ኃላፊነትዎ ከባድና ክፍተቱ ብዙ ቢሆንም የተሰጠዎትን ከመናገር በቀር ምንም አልሠሩም፤ ምክርዎም ከአማሳኞችና ከመናፍቃን ጋር ነው፤ ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ውጭ እስከ ሀገረ ስብከትና አጥቢያ ድረስ ወርደው ሥራ አስኪያጅ፣ ጸሐፊ እና ሒሳብ ሹም ይመድባሉ፤ የምንሾመው የሚያግዝ እንደራሴ ነው፤ አንድ ብቻ ሳይኾን ብዙ ሊያስፈልግ ይችላል፤ ከዚህ በፊትም በየዘመነ ፐትርክናው ሠርተንበታል" ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ "የሲኖዶስ" አባላት ፈሪ ሆኑ እንጅ ሰውየው የዚህን ያህል አስቸግረው ለቤተክርስቲያኗ ፈተና መሆናቸው ከታወቀና ለመመለስ ለመታረምም ፈቃደኛ አለመሆናቸው ከተረጋገጠ መፍትሔው እንደራሴ መሠረሙ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም እንደራሴ መሠየሙ ለዚህ ስር የሰደደና በስፋት ለተንሰራፋ ችግር መፍትሔ ሊሆን አይችልምና፡፡

መወሰድ የነበረበት እርምጃ በቤተክርስቲያኗ ሕግ ቀኖና ሥርዓት መሠረት ሰውየውን ማንሣት ወይም መሻር ነበረበት እንጅ እንደራሴ ብሎ ነገር ምን አመጣው፡፡ እንደራሴ የሚያስፈልገው ከዚህም በፊት ሲሠራበት የነበረው ፓትርያርኮቹ በሕመም ምክንያት ሥራቸውን መሥራት የማይችሉ ሲሆን፣ ሱባኤ የሚያበዙ ለሱባኤ ጽሙዳን ሲሆኑና ተመሳሳይ የሆነ

ጉዳይ ሲያጋጥም ነው እንጅ ሆን ብሎ በጥፋት ተግባር ላይ ተጠምዶ ቤተክርስቲያንን ለሚያደማ፣ ለሚወጋ፣ ለጥፋቷ ታጥቆ ለሚሠራ፣ ጠላትነቱን በግልጽ ላሳየ የጥፋት ልጅ አይደለም ተደርጎም አያውቅም፡፡ በቀኖና ቤተክርስቲያን መሠረት ደፍረው ይሄንን ማድረግ ቢያቅታቸው ነው እንደራሴያችንን እንሾማለን የሚልን ነገር ያመጡት፡፡ ኃላፊነታቸውን መወጣት ተስኗቸዋል፡፡

"የሲኖዶሱ" አባላት ይባስ ብለውም አባ ማትያስ በቤተክርስቲያን ላይ ከህደት ፈጽመው ቅጥረኛ ሆነው የሚሠሩለትን አካል "ተወካይ ይምጣልኝ" ሲሉ ተስማምተው እንዲገኝ መፍቀዳቸው ነው አስገራሚው ነገር፡፡ ቀድሞ ነገር አባ ማትያስን ሕግ እንዲጥሱ ጥፋት እንዲሠሩ የሚያደርጋቸው ማን ሆነና ነው ይምጣንኝ ካሉት አካል የቤተክርስቲያንን ሕግ በሚጻረር ሁሌታ ተወካይ እንዲገኝ ተስማምተው እንዲገኝ የተደረገው?

በሲኖዶስ ጉባኤ እንዲህ ያለ የሐሳብ አለመግባባት ሲያጋጥም በድምፅ ብልጫ የሚወሰንበት አሠራርና ሕግ አለ አይደለም ወይ? በውሳኔ አስተላለፍ ላይ ባንድ የውሳኔ ሐሳብ የተሰጠው ድምፅ እኩል በእኩል ሆኖ ለግልግል ቢያስቸግር እንኳ ጉዳዩን እንዴት ሊፈቱት እስከሚያስችል ድረግ ሔዶ ሕጉ ጥርት ብሎ የጠቀመጠና ጉዳዩን በዚህ አሠራ መፍታት እየቻሉ ቀኖና ቤተክርስቲያን ይፈቅድ ይመስል ወይም ደግሞ አገዛዙ ቤተክርስቲንን ለማጥፋት ከቤተክርስቲያን ጠላቶች ጋር ተባብሮ እየሠራ ያለ እንጅ እንደ ቀድሞው ዘመን ለቤተክርስቲያን ጥቅም የቆመ፣ የሚቆረቆር፣ የሚተጋ መንግሥት ያለን ይመስል የአገዛዙ ተወካይ ገላጋይ እንዲሆን ፈቅዶ መጋበዝን ምን አመጣው?

እነዚህ አባቶች የማይፈጽሙትን ነገር ለምን ይጀምራሉ? ወይ በራድ ይሁኑ! ወይ ደግሞ ሙቅ ይሁኑ! ለብ ያሉ ሆነው ለምን ለሰውም ለእግዚአብሔርም አስቸጋሪ ይሆናሉ? ይሄ ከእግዚአብሔር አፍ መተፋትን እንጅ ምን ያተርፍላቸዋል? ላይዘልቁበት አንድ ነገር እየጀመሩ በተደጋጋሚ ማሳፈሩ አይሰለቻቸውም ወይ?

እነዚህ አባቶች ይሄንን ማድረግ ማለት ቤተክርስቲያንን ማስደፈር ሥልጣኗን፣ ጥቅሟን፣ መብቷን አሳልፎ መስጠት መሆኑን፣ "መንግሥት በሃይማት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም!" የሚል ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ያለና ጥሪውን ወይም ግብዣውን ሲያቀርቡ ይሄንን ድንጋጌ መጻረር መሆኑን፤ አገዛዙም ይሄ ድንጋጌ አለበትና ጣልቃ ለመግባት ሕግ እንደሚከለክለው እንደሚያግደው የገዛ ሕጉን ማፍረስ መፃረር እንደሚሆንበት አጥተውት አይደለም የተስማሙት፡፡ ነገር ግን "አይሆንም! አይደረግም!" ቢሉም ማስቆም መከላከል እንደማይችሉ እነሱም ልብ ድፍረት እንደሌላቸው ከ 25 ዓመታቱ ልምዳቸው ጠንቅቀው ያውቃሉና "አስቁመን የማናስቆመውን ነገር አይሆንም! ብንል ትርፉ ለራሳችን ጣጣ መጋበዝ ነው" ብለው ስላሰቡ ነው ጣልቃ ገብነቱን የፈቀዱት፡፡

ሲጀመር ከ 24 ዓመታት በፊት ሕጋዊውን ፓትርያርክ አሰድዶ አባ ጳውሎስን፤ አባ ጳውሎስ ሲሞቱ ደግሞ እዚህ ያሉት አባቶች የተሰደዱትን አባቶች ለመመለስ ከተሰደዱት አባቶች ጋር እያደረጉት የነበረውን ሽምግልና ዐይን ባወጣ ጣልቃ ገብነት "የተሰደዱትን እንመልሳለን! እናስማማለን! የሚሉ ቄሶችን እንሰቅላለን!" ብሎ እስከመዛት ደርሶ ሽምግልናው እንዲቋረጥ ካደረገ በኋላ አባ ማትያስን የሾማቸው ማን ሆነና?

ይሄ ሁሉ ሲሆን ሲኖዶስ ነኝ የሚለው አካል ይሄንን መከላከል ካልሆነ ደግሞ "ቤተክርስቲያን ለጣለችብን አደራ ታማኝ ሆነን ነፍሳችንን አሳልፈን እንሰጣለን እንጅ አደራችንንማ አልበላም!" ብለው ዋጋ ሲከፍሉ ዓይተናል ወይ?

እናም አቅማቸው፣ ልባቸው፣ የእምነት ጽናታቸው ምን ድረስ መሆኑን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፣ ለተጣለባቸው አደራ ያላቸው ታማኝነት የማያወላዳ አለመሆኑን ስለሚገነዘቡ ነው ጣልቃገብነቱን የፈቀዱት፡፡

የገረመኝ በቤተክርስቲያን ጉዳይ ላይ ጣልቃ ገብቶ እንደፈለገው ማገንፋት ለወያኔ አዲስ ነገር ይመስል ጥቂት የማይባሉ ግለሰቦች በየ ድረገጹ **"እንዴ! ሕገ መንግሥቱ... እያለ መንግሥት ጥሪውን ተቀብሎ ሊገኝ ነው እንዴ!"** ምንትስ እያሉ ሲያሽቃብጡ ማየቴ ነው፡፡

ለመሆኑ ሲጀመር “ሲኖዶስ” ኃላፊነት ተሰምቶት፣ ልብ ኖሮት ይሄንን 25 ዓመት የቤተክርስቲያኗ ጥቅም ቅድሚያ እንዲሰጠው ሞክሮ አይደለም አስቦም አያውቅም እንጅ መቸ ነው የወያኔና የመናፍቃኑ ጥቅም እያለ ይሄንን ውድቅ አድርጎ የቤተክርስቲያንን ጥቅም የሚያስጠብቅ ውሳኔ አሳልፎና እሱንም አስፈጽሞ የሚያውቀው? በዚህ 25 ዓመት ቤተክርስቲያኗ ለገጠማት ችግርና ፈተና ሁሉ እንዳለው ሥልጣንና ኃላፊነት ግንባር ቀደም መፍትሔ ሰጭና ደራሽ ሆኖ በመገኘት ሲገባው ቤተክርስቲያኗ በፈተናዎችና መከራዎች መዓት ስትመሰቃቀል ዓይቶ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ እየሆነ ቤተክርስቲያንን ሲያስጠቃ ሲያስደፍር ጥቅሟን ሲያሳጣ የኖረው ማን ነውና?

ጥቂቶቹን እስኪ እንጠቃቅስ፡- የአራት ኪሎዎቹ አባቶች ቡድን ወያኔ እንደፈለገ የማያሽከረክራቸውና ቤተክርስቲያንን እየጎዱ የወያኔን ጥቅም የማያስጠብቁ እውነትም የሚያገለግሉት ቤተክርስቲያንን ከሆነ እዚሁ በሀገራችን ምድር በተለያዩ ሀገረ ስብከቶች ተማሪዎች “ማተብ ማሰር አትችሉም!” ተብለው ማተባቸው ካንገታቸው እየተበጠሰ በመጣሉ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ድርጊቱን ማስቆም ባለመቻላቸውና ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ “ሲኖዶስ” ለተባለው ሲያመለክቱ ሲኖዶሱ እንዳለበት ኃላፊነት ይሄንን የአረማዊያን የጥፋት እርምጃ ሰምቶ መውሰድ ያለበትን እርምጃ መውሰድ ሲገባው ምን ያደረገው ነገር ነበር?

ሕገ መንግሥቱ “ማንኛውም የእምነት ተቋም ለአምልኮ ከተፈቀደለት የማምለኪያ ስፍራ ውጭ በየ መንገዱ፣ በየ ሥራ ቦታው፣ በመንደር፣ ሕዝብ በሚሰባሰብባቸው ስፍራዎች ሁሉ ሃይማኖታዊ አስተምህሮውን በመስበክና አባላትን መመልመል ክልልክ ነው!” ብሎ እያለ እንዲሁም “የእምነት ተቋማትም ሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እርዳታንና የልማት ሥራዎችን ማለትም ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ጣቢያዎችን፣ ወፍጮ ቤቶችን የመሳሰሉትን አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን በመገንባት ለእምነት ማስፋፊያነት ወይም ዜጎችን ከነበሩበት ሃይማኖት አስወጥቶ ነጥቆ የራስ አባል ለማድረጊያነት መጠቀም የተከለከለ ነው!” የሚሉ ድንጋጌዎች እያሉ ማናፍቃኑ እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በመጣስ ቤተክርስቲያን ከነበራት የምእመናን ቁጥር ከግማሽ በላይ የሚሆነውን አግዘው ሲወስዱት ሲኖዶስ ነኝ ባዩ አካል ይሄንን ሕገ ወጥ አሠራርና ውንብድና በመቃወምና የሚመለከተው አካል ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ በማድረግ ምን የወሰደው እርምጃ ነበር? መናፍቃኑ ከአገዛዙ ጋር በመመሳጠር ውንብድናውን መፈጸማቸው ከታወቀም ሲኖዶስ ነኝ ባዩ አካል መንጋውን ቁጭ ብሎ ከማስበላት በስተቀር ኃላፊነቱን ከመወጣት አንጻር ምን የወሰደው እርምጃ ነበር?

በመላ ሀገሪቱ ከብዙ ዐሥርትና ምዕት ዓመታት በፊት አድባራቱ ከመንግሥታት የተሰጣቸውንና ይዞታቸው የሆነውን የመስቀልና የጥምቀት በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች አገዛዙ እንዳሻው እየነጠቀ ለመስጊድ መሥሪያና ለባለሀብት ሲያድለው ሲኖዶስ ነኝ የሚለው አካል ምን ያደረገው ነገር ነበር?

ቤተክርስቲያን ከንዋየ ቅድሳቶቿ የመጀመሪያው የሆነውን ዘፍ. 9፤8-17 የቃል ኪዳን ምልክቷን ትእምርተ ኪዳኗን (ሰንደቋን) አስወግጅና የኢጋንንት አምላኪዎች አርማ የሆነው ባለ አምስት ጎን ኮከብ የተለጠፈበትን የወያኔን ጨርቅ “መጠቀም አለብሽ!” ተብላ ስትገደድ ጉዳዩ ያሳሰባቸው ጳጳሳት ሔደው ቤተክርስቲያን ይሄንን ሰንደቅ (ትእምርተ ኪዳን) ንዋየ ቅዱስ ስለሆነ የምትጠቀምበት ከመንፈሳዊ አገልግሎት አኳያ መሆኑን በማስረዳት ኮከብ ሲለጠፍበት ግን ንዋየ ቅዱስ መሆኑ እንደሚቀር አስረድተው ከመጡ በኋላ የሚወጣው አዋጅ ቤተክርስቲያንን እንደማይመለከት ከተገለጸ በኋላ እንደገና አይሆንም ተብሎ በንዋየ ቅዱሷ ላይ የወያኔ ምልክት እየተለጠፈበትን እንድጠቀም ሲደረግና የመጀመሪያውን ንዋየ ቅዱስ እንድታጣ ሲደረግ ሲኖዶስ ነኝ ባዩ አካል ወያኔ በገዛ ሕገመንግሥቱ ያሰፈረውን “ማንኛውን የእምነት ተቋም ያለ መንግሥት ጣልቃገብነት የመሰለውን ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ ተቀብሎ የእምነት ሥርዓቱን በነጻ የመፈጸም መብት አለው” የሚለውን መብት አስጠብቆ በትእምርተ ኪዳኗ ከመጠቀም አኳያ ምን ያደረገው ነገር ነበር?

ርእሰ ገዳማት ዋልድባና ቅዱሳን አባቶች የአካባቢው ምእመናንም የቤተክርስቲያንን ክብርና መብት ለማስጠበቅ በሞከሩ ጊዜ የቤተክርስቲያንን ክብር እጅግ በተዳፈረና በናቀ መልኩ ግፍና በደል ሲፈጸምባቸው ለቤተክርስቲያን የቆመ በወያኔ የማይሽከረከር ሲኖዶስ ካለ ምን ያደረገው ነገር ነበር? ፤

በማቴ. 10፤40-42 ላይ የሰፈረውን የጌታን ቃል ለመፈጸም ሲሉ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያሉ ምእመናንና ካህናት ዝክረ ቅዱሳንን ሲዘክሩ ለምን ዘከራቹህ ተብለው ሲቀጡ ሲታሰሩ እንዳይዘክሩ ሃይማኖታዊ ትዕዛዛቸውን እንዳይፈጽሙ የሚከለክል ደንብ ተቀርጾ ሲከለከሉና ሲታገዱ ሲኖዶስ ነኝ ባዩ አካል ምን ያደረገው ነገር ነበር?

ወያኔ የቤተክርስቲያንን የደም ስር የሚቆርጡ ቤተክርስቲያንን ሳይሆን ወያኔን የሚያገለግሉ ካድሬዎችን ፓትርያርክና ጳጳሳት እያለ ሲሾም በወያኔ የማይሸከረከር ለቅድስት ቤተክርስቲያን የቆመ ሲኖዶስ ካለ ምን ያደረገው ነገር ነበር? ፣ እነኝሁ ጳጳሳትና ፓትርያርክ ተብየዎች ቅድስት ቤተክርስቲያንን በሙስና አዘቅት ውስጥ ሲያሰጥሟት በብልሹ አሥተዳደር ሲያጨማልቋት እንዳለው ሥልጣንና ኃላፊነት ሲኖዶስ ተብየው ምን ያደረገው ነገር ነበር?

ቤተክርስቲያንን ለውድቀት ለኪሳራ ለዳረጓትና ለሞትም ሊያበቋት ለደረሱት ለእነዚህና ላልጠቀስኳቸው እጅግ በርካታ የቤተክርስቲያን ችግሮች ሁሉ ሲኖዶስ ምን ያደረገው ነገር ነበር? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ምንም! የሚል ነው፡፡

አሁን ይሄ ሁሉ ጥፋታቸው ተሰምቷቸው ቆጭቷቸው ከዚህ በኋላ የቤተክርስቲያንን ጥቅም ለማስጠበቅ ቆርጠው ተነሥተው ከሆነ ይሄንን ወደፊት የምናየው የምናረጋግጠው ጉዳይ ይሆናልና ለዚህ እንቅስቃሴያቸው ቅርብ ሆነን ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ቢሆንም አሁን ቸኩለን "ጎሽ አባቶቻችን እንዲህ ነው እንጅ!" ብለን አናመሰግንም፡፡ ከቆይታ በኋላ የምናፍርበትን ውዳሴ አንለግስም፡፡ "የሚያድግ ጥጃ ከገመዱ!" ይባላልና እኔ በበኩሌ እንዲህ ያዝ ለቀቅ እያደረጉ፣ ፈራ ተባ እያሉ፣ ዋነኛውን የችግሩን አካል የወያኔን ጣልቃገብነት ሕገ ቤተክርስቲያንን በመፃረር መልኩ የፈቀዱና መፍትሔም ከእሱ እናገኛለን ብለው ከሚያምኑ አምነውም የሚጋብዙ የሲኖዶስ አባላት ጉባኤ ምንም ዓይነት አቋምና ጥያቄ ይያዙ የትም ይደርሳል የሚል እምነት የለኝም፡፡

ይጋበዝ የተባለው የአገዛዙ ባለሥልጣንም ተገኝቶ የሠራው ሥራ ይሄንኑ ነው፡፡ ሲኖዶስን ያህል ያለ እግዚአብሔር አለቃ አዛዥ ናዛዥ የሌለውን የቤተክርስቲያን ከፍተኛ አካል ምንም እንደማያውቅ ሕፃን ቆጥሮ "አድርጉ! አታድርጉ!" እያለ ሽንገላ የተሞላበት ትዕዛዝ በመስጠት የተያዘውን ወቅታዊና አንገብጋቢ የመወያያ ርእስ (አጀንዳ) በድርጅታዊ አሠራራቸው ይሄንን ጥያቄ ያነሡትንና ጠንካራ አቋም ያላቸውን አባቶች ከፋፍለው አስፈራርተው ወይም አባብለው አግባብተው የተነሣውን ጥያቄ አዳፍነው ለማስቀረት እንዲችሉና ለዚህም በቂ ጊዜ ለማግኘት ከወራት በኋላ በሚኪያሔደው ሌላ ጉባኤ እንዲታይ በመምከር ወይም ትዕዛዝ በመስጠት ነው አጃጅሏቸው የወጣው፡፡

ልዑል እግዚአብሔር የአባቶቻችንን ልብ በእምነት አጽንቶ የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት አስችሎልን ከልጆቻቸው ከሕዝበ ክርስቲያኑ ጋር በአንድነት ለቤተክርስቲያን በመቆም ቤተክርስቲያንን ከጥፋት ለመታደቅ ያበቃን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

***http://www.ethiopanorama.com***